# <u>ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ መመሪያ መጽሐፍ የግብ መምቻ ቀመር</u>



አለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል፣
የዩ ኤስ የንግድ ምክር ቤት አካል

ዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል የዩ ኤስ አሜሪካ ንግድ ምክር ቤት አካል ሲሆን እ.ኤ.አ በ1983 ዓ.ም የግል ንግድ እንቅስቃሴንና ገብያ ተኰር ለውጥን በአለም ዙሪያ ለማስፋፋት የተቋቋመ ማዕከል ነው። የናሽናል ኤንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ ዋንኛ ተሳታፊ እንደመሆኑ አለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራዝ ማዕከል በነፃ ገብያ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲ እንዲዳብር ማንኛውንም አይነት ድጋፍ ያደርጋል። በዮ ኤስ አሜሪካ አለም አቀፍ የልማት መ/ቤት፣ በግል ኮርፖሬሽኖችና ፋውንዴሽኖችም ይደገፋል። አለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ተቋም ከተመሰረተ አንስቶ በ80 ሀገራት ውስጥ ለተከናወኑ 700 ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። በንግድ ድርጅት አመራር ላይም የተለያዩ የስልጠና ፕሮግራሞችን በአፍሪካ፣ ኤሺያ፣ ማዕከላዊና ምስራቅ አውሮፖ፣ አውሮ-ኤሽያ፣ ላቲን አሜሪካና በመካከለኛው ምስራቅ አካሄዷል።

ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ መመሪያ መጽሐፋ
@ 2002 እ.ኤ.አ. ዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይስ ማዕከል

በድረ-ገጽ www. cipe. org ላይ ታገኙታላችሁ።

ምስጋና፣

ጆን.ዲ.ሱሊቫን፣ ፒ.ኤች.ዲ
ዋና ዳይሬክተር

ካተኽሪን ኩችታ-ሄልብሊንግ፣ ፒ.ኤች.ዲ
ደራሲና የላቲን አሜሪካ የምርምር ውክልና ፕሮግሪም ኃላፊ

ጂአፍ ገኸርትስ
ደራሲና የግምገማ ኃላፊ

ጆን ኤ. ዜምኮ
የመገናኛ ዳይሬክተር

ጆረግ አምሴለ
የፓብሊክ ጉዳይ አስፈፃሚ ዳይሬክተር

ጀኒፈር ቸኢንኤር
የድረ-ገጽ /ግራፊክ አርቃቂ

የአለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል 1155፣ 15ኛ መንገድ፣ ኤን ደብሊው
ሲዊት 700
ዋሽንግተን ዲ.ሲ 2005 / እ.ኤ.አ./
ስልክ 202/721 9200
ፋክስ 202 /721 9250
ኢ-ሜል cipe@cipe.org
ድረ-ገጽ www. cipe. org

# ማውጫ

<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

*<u>መግቢያ</u>*

ክፍል 1፣ **መቅረብና ማስተባበር**

1.1 ቁልፍ የብሔራዊ ቢዝነስ መሪዎች መሰብሰብ
1.2 የቢዝነስና የንግድ ማህበራትን ማግኘት

ክፍል 2 **የአትኩሮት ቡድኖች**

2.1 የአትኩሮት ቡድኖችን ማደራጀት
2.2 የአትኩሮት ቡድኖችን አወያይ መምረጥ

ክፍል 3፣ **የአትኩሮት ቡድን ስብሰባዎችና የስብሰባ ቦታ**

3.1 ቀንና ቦታ
3.2 የአትኩሮት ቡድኖችን መምራት፡፡

ክፍል 4፣ **ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳን መንደፍ**
ክፍል 5 **አስተያየት መሰብሰብና ክለሳ**

5.1 ከንግዱ ማህበረሰብ አስተያየት ማግኘት
5.2 አጀንዳውን መከለስና ለማስጸደቅ ማሰራጨት

ክፍል 6 **ህትመትና ስርጭት**

6.1 አጀንዳውን ማተም
6.2 ስለብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳው ማብራሪያ ማቅረብ፡፡

**የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ቁልፍ ጉዳዮች**

- ቁልፍ የሆኑ ብሔራዊ የቢዝነስ መሪዎች ማደራጀት፣
- በንግድ ድርጅት ዓይነት መሳተፍ
- የአትኩሮት ቡድን ስብሰባዎች አመራር
- የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳን መንደፍ
- ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ንግኙነት ማድረግና ሀሳብ መሰብሰብ
- አጀንዳውን እንደገና ማጤን
- አጀንዳውን በማስራጨት ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ
- አጀንዳውን ማሳተምና ማብራራት
- የመገናኛ ስልቶች፡፡

የብዙ ሀገራት የቢዝነስ ማህበራት የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የስነ መንግስትና ምጣኔ ሀብት ለውጦችን ለማምጣት በሚረዳ መልኩ ተጠቅመውበታል፡፡ በብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ አማካኝነት የግሉ ክፍል በቢዝነስና በምጣኔ ሃብት የእድገት መሰናክሎች ላይ እንዲያተኩርና ሙስናን ያልተደራጀውን የንግድ ክፍልና የቁጥጥር ማነቆን ለማስወገድ የሚረዱ መፍትሔዎችን ለመለየት ተጠቅሞበታል፡፡

## *መግቢያ*

*የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ የንግዱ ማህበረሰብ መዋዕለንዋይ እንዲያፈስ ለንግድ እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ እድገት አንዲበረታና እንዲነሳሳ የሚረዳው ጠቃሚ መሳሪያ ነው፡፡ የቢዝነስ አጀንዳ የንግዱ ህብረተሰብ ክህሎቱን ተጠቅሞ የህግና የቁጥጥር ቅድሚያ ጉዳዩችን በመለየትና ለፖሊሲ አውጪዎች በማመላከት በመንግስት ፖሊሲ ላይ ጫና እንዲያደርግ ያንቀሳቅሰዋል፡፡*

*ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳዎች የንግድ እንቅስቃሴን የሚያውኩ ህጐችንና መመሪያዎችን ለይተው በማመላከት እነዚህን መሰናክሎች ለማስወገድና የንግዱን ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ተጨባጭ መፍትሔዎችንና የለውጥ እርምጃዎችን ያመላክታሉ፡፡ የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ማዘጋጀት የግሉ ክፍል እንቅስቃሴውን የሚመለከቱ መንግስታዊ ፖሊሲዎች ላይ እውቀት እንዲኖረው ያስተምረዋል፣ የንግዱን ህብረተሰብ የሚመለከቱ ጉዳዩችን በአንድነት ለመንግስት ባለስልጣናት ለማቅረብ ከመርዳት አልፎ የንግዱ ህብረተሰብ አጀንዳ ድንጋጌ የመሆን እድሉን ያስፋዋል፡፡ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳዎች የልማት እንቅስቃሴ እንቅፍቶችን በማስወገድ ረገድ ውጤታማ መሳሪያነታቸው በአለም ዙሪያ በሚገኙ እንደ ማላዊ፣ ነይጀሪያ፣ ፖራጓይ፣ ፔሩ፣ ሮማንያ እና አሜሪካን በመሳሰሉት ሀገራት ተፈትነዋል፡፡*

*የቢዝነስ አጀንዳ ለማዘጋጀት ቁልፉ ነገር ተጨባጭ የሆኑ ክልላዊና የእንቅስቃሴ መስክ ፍላጐቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት መቻልና በመጨረሻ ጊዜ አጀንዳው የንግዱ ማህበረሰብ የራሱ መሆኑን እንዲገነዘብ ማስቻል ነው፡፡ የቢዝነስ መሪዎች አያሌ የተለያዩ የቢዝነስ ቡድኖችን የማደራጀትና በአብይ ጉዳዩች ላይ የጋራ አቋም ሊወሰድ የሚችል ህብረት የመመስረት ተነሳሽነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡*

*የመደረጃት ነፃነትና ለመንግስት አቤቱታ የማቅረብ መብት ለዲሞክራሲያዊ ተቋማት ማሰረታዊ ጉድዮች ናቸው፡፡ ገና በጀምር ላይ በሚገኙ የዴሞክራሲ ስርዓቶችም ቢሆን መሰረታዊ ህብረቶችን ማደራጀትና በጋራ የለውጥ ፍላጐት ላይ ተመስርቶ በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ተፅንኦ ማድረግ ይቻላል፡፡ የቢዝነስ ማህበራት መሰረታዊ ገብያ ነክ ፖሊሲዎችን ለማራመድ በተናጠል ከሚንቀሳቀሱ ይልቅ በአንድነት ቢንቀሳቀሱ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ የአለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራዝ ማዕከል ይህን የመመሪያ መጽሐፍ ያዘጋጀውም ለቢዝነስ ማህበራት፣ ለሙያ፣ ማህበራትና ለሌሎችም ፍላጐት ላላቸው ቡድኖች የብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችል የሚያሳዩ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መመሪያዎችን ለማመላከት ነው፡፡*

## ክፍል 1፣ መቅረብና ማስተባበር

### 1.1 ቁልፍ ብሔራዊ የቢዝነስ መሪዎችን መሰብሰብ

- ጉዳዮ የሚመለከታቸው ቁልፍ ግለሰቦች የቢዝነስ አጀንዳውን ንድፍ የሚመረምርና የሚተች የአማካሪ ኮሚቲ ለመመስረት መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

የአጀንዳው የኃላ ኃላ ግብ መምታት ከቢዝነስ ማህበረሰቡ የጐላ ተሳትፎ ጋር እጅግ የተቆራኝ ነው። ብዛት ባለው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አባላት አጀንዳው በተወገነ ቁጥር ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት አትኩሮትንም ያገኛል።

- የፕሮጀክት አስተባባሪ መምረጥ
  የፕሮጀክት አስተባባሪው የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ለማዘጋጀት ሙሉ በሙሉ እራሱን ያዘጋጀና የዳበረ የአመራርና የአስተዳደር ክህሎት ያለው ሰው መሆን ይኖርበታል።

- የስብሰባው ተሳታፊዎች በስብሰባው ለመሳተፍ ይፈልጉ የሆናል የሚላቸውን የተለያዩ ዘርፎች፣ ክልሎች፣ የግል ማህበራት ዝርዝር ማዘጋጀት የኖርባቸዋል።
  ብዙ የግል ባለሀብቶች የቢዝነስ ማህበራት አባላት ናቸው። ስለሆነም የማህበራት መሪዎችን መቅረብና ማግኘት ድጋፋቸውን ለማግኘት የሚያስችል ወሳኝ መንገድ ነው።

- የተወሰኑ የአማካሪ ኮሚቴ አባላት ከማህበራት ጋር በተወሰነ ቀን ተገናኝተው የማህበራቱን የተሳትፎ ፍላጐት ማሳካት እንዲችሉና ውጤቱንም ለፕሮጀክቱ አስተባባሪ ሪፖርት እንዲያደርጉ አድርጐ መመደብ /መሰየም ያስፈልጋል።

### 1.2 የቢዝነስና የንግድ ማህበራትን ማግኘት።

- ከላይ በ1.1 የቢዝነስ ማህበራትን አመራር ለመገናኘት የተስማሙ የአማካሪ ኮሚቴ አባላት ይህኑ ግንኙነት የማድረግ ተግባር መጀመር ይኖርባቸዋል።

  የአማካሪ ኮሚቴው አባላት ከቢዝነስ ማህበር መሪዎች ጋራ በሚገናኙበት ጊዜ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ የማዘጋጀትን ጥቅምና የእንቅስቃሴ ደረጃዎችን ሊገልጹና ሊያብራሩላቸው ይገባል። የቢዝነስ መሪዎች የቢዝነስ መሰናክሎችን ለማስወገድና የቢዝነስ ከባቢ አየርን ለማስተካከል አብረው ለመስራት ያቀዱ መሆኑ ቁልጭ ብሎ መገለጽ አለበት። የአባሎቻቸው ፍላጐት ምን እንዲሆን ይደረስበት ዘንድ የእያንዳንዱ ማህበር ተሳትፎ ወሳኝ ነው። አጀንዳውን በመጻፍ፣ በመከለስና ዋናውን ሰነድ በማፅደቅ ድምፅ የሚኖራቸው መሆኑ በአፅንኦት ሊነገራቸው ይገባል። የሚጸድቀው የቢዝነስ አጀንዳ ለርዕሰ-መንግስቱ፣ ቁልፍ ለሆኑ ባለስልጣናት፣ ለህዝቡና ለሚዲያ ይቀርባል።

- በሂደቱ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑ የቢዝነስ ማህበራት መሪዎች ስብሰባ ለማድረግ ፍቃደኛ መሆናቸው መጠየቅ አለበት።

- እያንዳንዱ የአማካሪ ኮሚቴ አባል ለፕሮጀክት አስተባባሪው የየትኛው ማኅበር መሪዎች ለመሳተፍ የየትኛው ደግሞ ስብሰባ ለማድረግ ፍላጐት እንዳላቸው በሪፖርት መልክ ማቅረብ አለበት።

## ክፍል 2 **የአትኩሮት ቡድኖች**

| |
|---|
| የአትኩሮት ቡድን ማለት ምን ማለት ነው ?<br><br>የአትኩሮት ቡድን በኮሚቴ ውስጥ የሚገኝ ኮሚቴ ነው። የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ለማዘጋጀት ማህበራት ፕሮጀክቱን የሚመራ ኮሚቴ በማቋቋም ይጀምራሉ። የተለያዩ ዘርፎችንና ክልሎችን ለሚወክል ትልቅ ማህበር አንድ ኮሚቴ የሁሉንም የማህበሩን አባላት ብሶትና ፍላጐት በብቃትና በአግባቡ ሊያንፀባርቅ አይችልም። በመሆኑም የእያንዳንዱን ዘርፍ፣ ክልል ወይም ጉዳይ የሚወክሉ ንዑስ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ። እነዚህ ንዑስ ኮሚቴዎች በተወሰነ የፖሊስ መስክ ላይ በማተኮር የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ክፍል የሚሆን የራሳቸውን ንድፍ ያዘጋጃሉ። የቁጥጥር ኮሚቴው በንዑስ ኮሚቴዎች የተነደፉትን ክፍሎች በማሰባሰብ የመጨረሻውን የአጀንዳ ሰነድ ያዘጋጃል። ለዚህም ነው ንዑስ ኮሚቴዎች ወይም የአትኩሮት ቡድኖች ጠቃሚ የሚሆኑት። |

### 2.1 **የአትኩሮት ቡድኖች ማደራጀት**

- የአትኩሮት ቡድኖች መቋቋምና የቢዝነስ ማህበራት መሪዎችንም በስራ መስካቸው አይነት ወይም ክልላቸውን መሰረት በማድረግ በቡድን በቡድን ማደራጀት ይገባል። እያንዳንዱ የአትኩሮት ቡድን አላማው አንድ ነው። ማለትም የቢዝነስ እንቅፍቶችን መለየትና መፍትሔ መጠቆም።

ተመሳይ የስራ መስክን ወይም የክልልን ጥቅም የሚጋሩ የቢዝነስ መሪዎችን በተለያዩ ቡድኖች ማደራጀት እያንዳንዱ ተሳታፊ በራሱ ጉዳዮ ላይ እንዲያተኩርና የዋናውም አጀንዳ አደረጃጀት ቀላል እንዲሆን ይረዳል።

የተወሰኑ የቢዝነስ ማህበር መሪዎች ከአንድ የአትኩሮት ቡድን በላይ ለመሳተፍ ከፈለጉ ይችሉ ይሆናል። በእርግጥ ይህ ተቀባይነት ያለውና የግል ክፍሉን ተሳታፊነት የሚያጠናክር ነው። ነገር ግን የአትኩሮት ቡድኖች መጠን ውሱን መሆን ይኖርበታል። ጥቂት አባላት ያሉት ቡድን የንግዱን ህብረተሰብ በሚገባ እንደማይወክል ሁሉ ብዙ አባላትን ያቀፈ ቡድንም አትኩሮት አልባና ውጤት አልባ የመሆን እድል ይኖረዋል። የአትክሮት ቡድኖች ቁጥር የሚወሰነው በሂደቱ ለመሳተፍ በተሰማሙ የቢዝነስ ማህበራት መሪዎች ቁጥርና በተወከሉ ክልሎችና ዘርፎች ብዛት ነው።

### 2.2 **የአትኩሮት ቡድን አወያዮችን መምረጥ**።

- የእያንዳንዱ የትኩሮት ቡድን የስብሰባ አወያይ መምረጥ አለበት። አወያዮ የቡድኑ ስብሰባ ቁልፍ የቢዝነስ እንቅፋቶችን በመለየትና መፍትሔ በመስጠት ላይ ያተኮረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ግለሰቡ የአትኩሮት ቡድን

አባላት ወይም የአትኩሮት ቡድን አባላት የመጡበትን ክልል ወይም የቢዝነስ እንቅስቃሴ አይነት የተረዳ ሰው መሆን አለበት።

- የፕሮጀክት አስተባባሪው ለእያንዳንዱ ስብሰባ አወያይ የአትኩሮት ቡድን አባላትን ዝርዝርና አድራሻ መስጠት ይኖርበታል።

## ክፍል 3 ስብሰባዎችና የመገናኛ ቦታ

የአትኩሮት ቡድን ስብሰባ ማመሳከሪያ

- የስብሰባ ቀንን መወሰን
- ተስማሚ የስብሰባ ቦታ መምረጥ
- የስብሰባ አጀንዳ ማዘጋጀት
- ለስብሰባ ተሳታፊዎች ጥሪ ማድረግና የስብሰባ አጀንዳውን ቀድሞ እንዲደርሳቸው ማድረግ
- የየስብሰባ ተሳታፊዎችንና የሚያስፈልጉ ማተሪያሎችን /ጥራዞች የማስታወሻ ደብተር፣ እስክርቢቶዎች/ ዝርዝር ማዘጋጀት
- ለስብሰባ ተሳታፊዎች ቡና፣ ሻይና የለስላሳ መጠጦችን ማቅረብ
- እንቅፍቶችና መፍትሔዎቻቸውን መመዝገብ።

### 3.1 ቀናትና ቦታዎች

- የፕሮጀክት አስተባባሪው የሁሉንም ስብሰባዎች ጊዜአዊ ፕሮግራም ማዘጋጀት አለበት።

- የቢዝነስ ማህበር መሪዎች በስብሰባው ለመገኘት ማቀድ እንዲችሉና ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲኖር የእያንዳንዱ አትኩሮት ቡድን የስብሰባ ቀን ተወስኖ ቀድሞ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል። የፕሮጀክት አስተባበሪው በአያንዳንዱ የአትኩሮት ቡድን ስብሰባ ላይ መገኘት አለበት።

- የፕሮጀክት አስተባባሪው የስብሰባ ፕሮግራሞችን ለእያንዳንዱ አወያይ ማሳወቅ አለበት።

- እያንዳንዱ አወያይ የማህበር መሪዎችን ፍላጐት ከግምት ውስጥ አስገብቶ የአትኩሮት ቡድናቸውን የስብሰባ ቦታ ይመርጣል።

- አወያዮች የቢዝነስ መሪዎች አባሎቻቸውን ለስብሰባው እንዲያዘጋጅ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣሉ። የማህበር አባላት ስለ የቢዝነስ አጀንዳው ዕቅድ እንዲነገራቸውና በንግድ እንቅስቀሴው ላይ የተጋረጡ መሰናክሎችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን እንዲሰነዝሩም መጠየቅ ይሮርባቸዋል።

- የፕሮጀክት አስተባባሪው የስብሰባ መዝገቡን ለአማካሪ ኮሚቴ አባላት ማስራጨት አለበት።

### 3.2 የአትኩሮት ቡድኖችን መምራት።

የእያንዳንዱ የአትኩሮት ቡድን ግብ በተወሰነ የንግድ ዘርፍ ወይም ክልል በቅድሚያ መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮችና የተጠቆሙ መፍትሔዎችን ዝርዝር ማዘጋጀት መቻል ነው::

- አወያዩ ስብሰባውን የሚጀመረው የስብሰባ አጀንዳዎችን በማሰራጨትና የስብሰባው ተሳታፊዎች የስብሰባ አላማ እንቅፋቶችን በቅደም ተከተል በመለየት ለውጥ ለማምጣት የሚችሉ አስተያየቶችን መስጠት መሆኑን በማሳሰብ የሆናል::

- አወያዮ በስብሰባው ላይ የተጠቀሰ ማንኛውም አይነት እንቅፋትን መመዝገብ አለበት::

- እያንዳንዱ የስብሰባ ተሳታፊም የተጠቀሱ መሰናክሎችን እንደቁም ነገራቸው ቀደምትነት መመዝገብ አለበት::

- አወያዮ ስብሰባው በየመስኩ ካነሳቸው ጉዳዮች መካከል ከፍተኛ ቅድመ-ቁምነገር ያላቸውን ለይቶ ይይዛቸዋል::

<table>
<tr><td>

መሰናክሎችና የመፍትሔ አስተያየቶች

የፖራጉየ የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ<br>
ፌፕሪንኮ እ.ኤ.አ./1997/

**ጉዳዩ፤ ቀረጥ /ግብር/**<br>
**እንቅፋት፤**

የቀረጥ አስተዳደሩ ግልጽና ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ስርዓት ስለሌለው የንግድ ተቋማት ሁለትና ሶስት እጥፉ ቀረጥ እንዲከፍሉ በማድረግ ግብር ላለመክፈል መደበቅ፣ሙስናና ኢንፎርማል የንግድ እንቅስቃሴዎችን አስከትሏል::

<u>የፖሊሲ እርምጃ መፍትሔ</u>

መንግሥት የቀረጥ አስተዳደሩን አስመልክቶ ተጠያቂነትና ግልፅነት እንዲኖሩ የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰድና ከአቅም በላይ መገበርን ለማስቀም የሚረዳ አለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ስታንዳርድን በተግባር ላይ ማዋል ይኖርበታል::

<u>ስትራተጂዊ የቢዝነስ ማህበራት አንድነት</u>

አለም አቀፍ የአምራችነት ጥናቶች ማዕከል<br>
ሮማኒያ እ.ኤ.አ./1999/

**ጉዳዩ፣ የንግድ እድገት**

**እንቅፋት፤**

የጉምሩክ መ/ቤቶችን ለማስተዳደር አያሌ የመንግስት መመሪያዎች ሲኖሩ ከእነዚህም ውስጥ የተደጋገሙ፣ የሚቃረኑና በወጥነት የማይተገበሩ ህጐች ይገኙበታል:: የዚህም ውጤት መምታታት፣ የቀረጥ ጫና ሙስናና ብሎም የንግድ እንቅስቃሴ መገታትና የወጪ መጨመር ሆኗል::

</td></tr>
</table>

**ፖሊሲ ነክ የመፍትሔ**

የጉምሩክ መ/ቤት የሚገዛበት የመንግስት ህግ ቀላልና ግልጽ መሆን አለበት። ያረጁ፣ ተደጋጋሚና ተቃራኒ ሕጐችን ማስወገድና ሙስናንም ለመዋጋት የተጠናከረ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

- አወያዩ መንግስት እያንዳንዱን እንቅፋት ለማሰወገድ እንዲያቅድ የሚረዱ የመፍትሔ ሀሳቦችን የስብሰባው ተሳታፊዎች እንዲያውቁት መጠየቅ ይኖርበታል።

- ቀጥሎም አወያዩ ከተሰብሳቢዎቹ ጋር በመሆን በእያንዳንዱ ጉዳይ ስር በተሰነዘሩ የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ ውይይት እንዲደረግ ያደርጋል።
  የዚህ ውይይት አላማ እያንዳንዱን መሰናክል ለማሰወገድ ከተጠቀሱ የመፋትሔ ሃሳቦች መካከል የቡድን አባላቱ አጅግ አግባብነት አላቸው በሚሏቸው ላይ የጋራ ስምምነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

- አወያዩ የስብሰባ ውጤቶቹን ይዘግብና መዝገቡን ለፕሮጀክት አስተባባሪው የስረክባል።

**ፖሊሲ ሊያስቀድማቸው የሚገቡ**

**ዮ ኤስ የንግድ ምክር ቤት ፌዴሬሽን ኢ.ኤ.አ.**//1994/

ቀዳሚ ጉዳዮች

- ሚዛኑን የጠበቀ በጀት
- የተጨማሪ ሀብት ቀረጥን መቀነስ
- የቁጥጥር እርከኖችን መቀነስ
- የጡረታ ስርአትን የግል ማድረግ
- የጤና እንክብካቤ ስርዓትን መለወጥ
- የፍትህ ስርአቱን ማሻሻል
- መንግስታዊና ግላዊ ትብብርን ማሳደግ
- የኃይልና የመሬት አጠቃቀም መመሪያን ማሳነስ፣ የመገናኛና ትራንስፖርት አውታሮችን ማልማት።
- የነፃ ንግድ ስምምነቶችን ማፅደቅ።

***ለውጦች***

*ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ*
***የግብፅ ኢንዱስትሪዎች ፌዴሬሽን እ.ኤ.አ./2000/***
*የኤክስፖርት ስርዓቱን ለማሻሻል የተሰነዘሩ አስተያየቶች*

***ድርጅታዊ***

*የግብፅ የኤክስፖርት ንግድ ማስፋፊያ ማዕከልን /ኢ.ኢ.ፒ.ሲ/ የንግድ ውክልና ቢሮዎችን፣ ትሬድ ፖይንትትንና ትሬድ ኔትን ጨምሮ ቁልፍ የኤክስፖርት ወኪሎችን በአንድ ጣራ ስር ማድረግ፡፡*

*የጉምሩክ ሠራተኛውን ስልጠናና ደምወዝ ማሻሻል፡፡*

***መመሪያዊ***

*የመንግስት የሚኒስተር መ/ቤቶችንና የሌሎች መ/ቤቶችን ተደራራቢ ሚናዎች ማስወገድና ወጥና አሰሪ የሆነ የተግባር እቅድ መንደፍና ማዘጋጀት፡፡*

*የመቆጣጠር ስልጣን ከመሰጠቱ በፊት የሚመለከተው የመንግስት አካል ለሁሉም ደረጃዎች የኢኮኖሚያዊ እንድምታ ያላቸው ማብራሪያዎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡*

*የቁጥጥር መመሪያዎች ከመውጣታቸው በፊት የ60 ቀናት ጊዜ ግልፅ ውይይት መደረግ አለበት፡፡ ለሁሉም ትችቶች መልስ መስጠትም የግድ ነው፡፡*

*የቁጥጥር መመሪያዎችን አስፈላጊነትና ህቀኝነትን መስረት አድርጐ በፍርድ ቤት ለመሞገት የሚያስችል የአቤቱታ ሂደት ስርዓት መጣል አለበት፡፡*

***ፖሊሲዎች***

*በጉምሩክ ባለ ስልጣንና የንግድ ድርጅት ጥበቃና እንክብካቤ ቢሮ ተቀባይነት የሚኖረውና እንደ አለም አቀፍ የምስክር ወረቀትነት የሚፈለግ ለሁሉም የኤክስፖርት ንግድ ደንቦች የሚሆን አንድ ቅጽ ማዘጋጀትና የቀድሞ ቅጾችንና የማመልከቻ ወረቀቶችን ማስወገድ፡፡*

*የጉምሩኮች ባለስልጣን ዋና መ/ቤቶችን በየወደቦቹ ከሚገኙ ቅርንጫፍ ቢሮዎች ጋር ለማገናኘት የሚያስችል ኔትወርክ በመዘርጋት የጉምሩኮች ደንቦችን በዘመናዊ ቲክኖሎጅ መሰረት ላይ መጣል፡፡*

## ክፍል 4፡ የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ መንደፍና ማሰራጨት

- የፕሮጀክት አስተባባሪውና በአማካሪ ኮሚቴው ውስጥ የሚገኙ የቢዝነስ መሪዎች በሁሉም የአትኩሮት ቡድኖች ዋና ዋና ስለተባሉት እንቅፋቶች የመፍትሄ ሀሳቦችን ጨምቆ የሚያወጣ ግብረ ኃይል በመሰየም የአጀንዳው የመጀመሪያ ንድፍ እንዲዘጋጅ ማድረግ አለባቸው።

- የአጀንዳው መግቢያ የአጀንዳውን ምንነት፣ የሚሰጠውን ጥቅምና በቀረጻው እነማን እንደተካፈሉ ግልጽ አድርጎ ማሳየት አለበት።

- ቀጥሎም ግብረ-ኃይሉ በቅድሚያ ሊፈቱ ይገባቸዋል የሚባሉትን እንቅፋቶች ለይቶ ያስቀምጣቸው።
  በዚህ ውስጥ ለቢዝነስ እንቅስቃሴ መሰናክል ናቸው የሚባሉ ሕጎች ወይም መመሪያዎችና ለግሉ ባለሀብት ጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ሌሎች ጉዳዮች ትንታኔ መካተት ይኖርባቸዋል።

- ለእያንዳንዱ እንቅፋት ተጨባጭ መፍትሔ መጠቆም ያሻል።
  የመፍትሔ ሀሳቦች የመንግሥት ባለሥልጣናት ተለይተው የታወቁ እንቅፋቶችን በማስወገድ የንግድ እንቅስቃሴው የሚገኝበትን ሁኔታ ለማሻሻል እንዲችሉ የሚያመላክቱ መሆን ይኖርባቸዋል። ለፖሊሲ አውጭዎች አሳማኝና ሊተገበሩ የሚችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማቅረብ የቢዝነስ አጀንዳውን የማጽደቅ እድሉን ከፍ እንዲል ያደርገዋል።

- የአጀንዳውን ዋንኛ ጭብጥ ስለማጠቃለል።

  የአጀንዳው ጭብጥ ጠቅለል ብሎ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ሊያነበው የሚችል መሆን አለበት። የጭብጡ ማጠቃለያ የራሱ የሆነ አጠር ያለ መግቢያ ኖሮት በቢዝነስ እንቅስቃሴው የተጋረጡ እንቅፋቶችንና የተጠቆሙ የመፍትሔ ሀሳቦችን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል። አጠር ካለ ማጠቃለያ ጋር ከ4 እስከ 6 ገጾች መብለጥ የለበትም።

- የቢዝነስ አጀንዳው የርዕስ ማውጫ ሰንጠረዥ ሊዘጋጅለት ይገባል።

- ግብረ ኃይሉ የአጀንዳውን ጥራዝ አዘጋጅቶ ለፕሮጀክት አስተባባሪው መስጠት አለበት።

ፎቶ
8 section 4

## <u>የቢዝነስ አጀንዳ ንድፍ</u>
## ዩ.ኤስ አሜሪካ የንግድ ምክር ቤት ፌዴሬሽን
## /እ.ኤ.አ 1994/ የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ

### <u>የቁጥጥር ማሻሻያ</u>

**<u>ዓላማ፤</u>** ባለሀብቶችንና ተጠቃሚዎችን ከቁጥጥር ማነቆ ለማላቀቅና ብሎም ወደፊት የሚወጡ የቁጥጥር ደንቦች አላስፈላጊ ጫና ወይም ጉዳት እንዳያስከትሉ ለማድረግ በሚረዳ መልኩ የተቋማት ማሻሻያ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

**<u>ችግሩ፤</u>** የፌደራል የቁጥጥር ደንቦች ወደፊት ሊያስከትሉ የሚችሏቸውን አላስፈላጊ ጭነቶች ከግምት ውስጥ ስያስገቡ የሚዘጋጁና የሚጫኑ ናቸው፡፡ በተለይም ከሌሎች ደንቦችና የኤኮኖሚ ጉዳዮች ጋር እንዴት ሊጣጣሙ እንደሚችሉ በቅድሚያ ገንዛቤ አይወሰድም፡፡

**<u>መነሻ</u>** የመንግስት የነጻ ገበያ መመሪያ ጥሩም ይሁን መጥፎ የግለሰቦችንና የድርጅቶችን ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር የሚመለከት ነው፡፡ የመመሪያው ጫና በሚገርም ሁኔታ እየከፋ እስካሁን ድረስ በተግባር ላይ የዋሉት የቁጥጥር መመሪያዎች ያስከተሉት ስራ አጥነት፣ ኪሳራና የአገሪቱን ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት የጎዱት አልበቃ ብሎ የቢዝነስ ተቋማት አሁንም አዳዲስ ህጎች ይዘዋቸው ብቅ ከሚሉት የቁጥጥር መመሪያዎች ጋር ግብግብ እየገጠሙ ይገኛሉ፡፡ ካላስቆሚቸው በስተቀር አዳዲሶቹ የቁጥጥር መመሪያዎች የሸቀጦችን ዋጋ ከፍ ያደረጉትና የኤኮኖሚ እድገትንም ይገቱታሉ፡፡ ማርች 1992 /እ.ኤ.አ./ እንደታተመው የቁጥጥር የማኅበራዊ ወጪዎች ጆርናል ከሆነ ቁጥጥር የቢዝነስ ተቋማትን በዓመት ከ400 ቢሊዮን ዶላር በላይ አስወጥቷቸዋል፡፡

**<u>ሊወስድ የሚገባው እርምጃ፤</u>** አዳዲስ ህግጋት እንዳይወጡ በማድረግና ንግዱንና ተጠቃሚውን ባለማሰለስ በማጥናት የቁጥጥር እፍይታን ማምጣት፡፡

| የምክር ቤቱ አቋም | ሌላው አቋም |
|---|---|
| ኤኮኖሚው ከአንድ የታለመ የእድገት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድርሰ የሁሉንም አዳዲስ ህግጋት አፈጻጸም ማቋረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህም እነዚህን የቁጥጥር መመሪያዎች እንደገና ለማጤንና ንግዱንም ከሚያስከትሉበት ወጪ መከላከልን ለጊዜውም ቢሆን ተግባራዊ ለማድረግ እድል ይሰጣል፡፡ | አዳዲስ የቁጥጥር መመሪያዎች በስራ ላይ ከመዋል እንዲቆጠቡ ማደረግ የሚያመጣው የኤኮኖሚ ጥቅም እጅግም ነው፡፡ እንዲያውም ጤናና እንክብካቤን የሚመለከቱ መመሪያዎች እንዳይተገበሩ ያደርጋቸዋል፡፡ |

### <u>የውይይት ውጤት</u>

- ጥቂት አላስፈላጊ የሆኑ የቢዝነስ የቁጥጥር መመሪያዎች መኖር፡፡
- ሕግ አክባሪነት/ ሕጎችን በመተግበር ሳቢያ የሚከሰት ወጪ ይቀንሳል፡፡
- የአገሪቱ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ይጨምራል፡፡

# ክፍል 5፡ መረጃ መሰብሰብና ክለሳ

## 5.1. ከኅብረተሰቡ አስተያየት ማግኘት

- የፕሮጀክት አስተባባሪው የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ረቂቁን ለእያንዳንዱ ተሳታፊ ማኅበር እንደገና ያጤነው ዘንድ መስጠት አለበት፡፡

  የፕሮጀክት አስተባባሪው ማኅበራት በቂ ጊዜ ኖሯቸው ረቂቁን ከአባሎቻቸው ጋር በመሆን እንዲያዩትና አስተያየት እንዲሰጡበት የሚያስችል የአስተያየት መሰብሰቢያ የጊዜ ገደብ ሊያበጅ ይገባዋል፡፡

- የእያንዳንዱ ማኅበር መሪ የማኅበሩ አባላት የሰጡትን አስተያየቶች በመቀመር ለፕሮጀክት አስተባባሪው በተሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 5.2. አጀንዳውን መከለስና ማሰራጨት

- የፕሮጀክት አስተባባሪውና የግብረ ኃይሉ አባላት የተሰበሰበውን አስተያየት ከአጀንዳው ረቂቅ ጋር ያቀላቅሉት

- የፕሮጀክት አስተባባሪው የአጀንዳው የመጨረሻ ረቂቅ እንዲወጣና እንዲጸድቅ ለማድረግ የተከለሰውን ረቂቅ ለተሳተፉ የቢዝነስ ማኅበራት ሁሉ ማሰራጨት አለበት፡፡

<u>የፕሮጀክቱ አስተባባሪ</u> ከተስተካከለው የብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ረቂቅ ጋር እያንዳንዱ ተሳታፊ የቢዝነስ ማኅበር መሪ ፈርሞ በተወሰነለት ቀን የሚመልሰው የአፈጻጸም ቅጽ በአባሪነት ማሰራጨት አለበት፡፡

## ረቂቅ አጀንዳ

## የክፍት በሮች ዘመቻ

## ሮማኒያ እ.ኤ.አ./ /2000/

**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ አጀንዳ**

**ጉዳዩ፤**
**የቁጥጥር መመሪያዎች**

**ፖሊሲ ነክ የመፍትሔ አስተያየቶች**
ፍትሃዊ የገበያ ውድድር መኖሩንና በኤሌክትሮኒክስ መላላኪያ መንገድ የሚካሄድ ንግድ ተጠቃሚ ጥበቃን የሚያረጋግጥ ፀረ-ሙስና ህግ ማውጣት፡፡ ይህም ህግ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በተለይም በሰሜን አትላንቲክ ስምምነት ድርጅት የተመለከቱትን የሚመጥን መሆን ይኖርበታል፡፡

**ጉዳዩ፤**
**ግብር**

**ፖሊሲ ነክ የመፍትሔ አስተያየቶች**
ብዛት ያላቸው ሮማንያውያን ለግል ጥቅምም ሆነ ለንግድ አገልግሎት የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለመፍቀድ ይረዳ ዘንድ የተጨማሪ እሴት ግብርን ከ19% ወደ 5% እና የኮምፒውተርና የፕሮግራሞችን የግምሩክ ቀረጥ መቀነስ፡፡

**የቱሪስት ዘርፍ አጀንዳ**

**ጉዳዩ፤**
**የተደጋገሙ የንግድ ፈቃድ ደንቦች**

**ፖሊሲ ነክ የመፍትሔ አስተያየቶች**
የጉዞ ወኪሎችን የሚመለከቱ አስተዳደራዊ ደንቦችንና የንግድ ፈቃድ መስፈርቶችን እንደገና ማየትና ተደጋጋሚነት ያላቸውን ደንቦች መመሪያዎች ማስወገድ፡፡

**ጉዳዩ፤**
**አካባቢን የሚመለከቱ የቁጥጥር ህጎች**
**ፖሊሲ ነክ የመፍትሄ አስተያየቶች**
እንቅስቃሴያቸው አካባቢን የሚበክሉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተበከለውን አካባቢ የማጽዳት ኃላፊነት እንዲኖርባቸው የሚያደርግ ሕግ ከማውጣት ባሻገር የሮማኒያ የተፈጥሮ ሀብት በቱሪስቶች እንዲጎበኝ ለማበረታታት የሚያስችል ገንዘብ መመደብ፡፡

## ክፍል 6፡ ኅትመትና ስርጭት

### 6.1. ያለቀለትን አጀንዳ ማተም

- የፕሮጀክት አስተባባሪው ያለቀለትን የብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ጥሩ አድርጎ በመጽሔት መልክ ማሳተም አለበት፡፡

### 6.2. የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳን አዘጋጅቶ ማቅረብ

- ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት እቅድ ማውጣት፡፡

- የፕሮጀክት አማካሪ ኮሚቴው አጀንዳውን ለመንግሥት ባለስልጣናት፣ ለሚዲያና ለህዝብ የሚያቀርብበትን ቀን መወሰን አለበት፡፡

- የመገናኛ /መሰብሰቢያ/ ቦታ ስለመምረጥ፤
  አጀንዳውን ለባለስልጣናት፣ ለሜዲያና ለህዝብ ለማቅረብ ሜዲያ በብዛት በሚኖርበትና የመንግሥት ባለሥልጣናት በሚሰሩበት በዋና ከተማው ቢሆን ይመረጣል፡፡ ጥሩ የመገናኛ / መሰብሰቢያ ቦታዎች የሚባሉት በሕግ መወሰኛው ህንጻ ውስጥ ወይም ፊት ለፊት ወይም ህጋዊ ፈቃድ ከተገኘ በሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ቤት መንግሥት ውስጥ የሆኑ እንደሆን ነው፡፡ ካለበለዚያ ለመሰብሰቢያ ምቹ የሆነ በሕግ ማውጫው ጽ/ቤት አጠገብ የሚገኝ ሆቴል ለመገናኛ ቦታነት ሊመረጥ ይችላል፡፡

- የፕሮጀክት አስተባባሪው አጀንዳው በይፋ በሚቀርብበት ዕለት ለሚገኙት እንግዶች የግብዣ ወረቀት መበተን አለበት፡፡

- 
  የግብዣው ወረቀት የብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳው ለምን ጠቃሚ እንደሚሆን፣ ገለጻውን ማን እንደሚያደርግ፣ የአጀንዳው መቅረቢያ ቦታ፣ ጊዜና የፕሮጀክት አስተባባሪው ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥ የሚችልበት አድራሻ አጠር ባለ መልኩ መግለጽ አለበት፡፡

- የፕሮጀክት አስተባባሪው ከግብዣ ወረቀቱ ጋር የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳንና የአጀንዳውን የማጠቃለያ ጭብጥ ለሕግ አስፈጻሚውና ለሕግ አውጪው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ቁልፍ ለሆኑ የመንግሥት ባለስለጣናት መላክ አለበት፡፡

  የአማካሪ ኮሚቴው ቁልፍ የመንግስት ባለስልጣን አግኝቶ በብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳው ላይ ለመወያየትና አጀንዳው በይፋ በሚቀርብበት ዕለት እንዲገኙ ማበረታት/ መገፋፋት ይኖርበታል፡፡

## የሪፖርት ማመሳከሪያ

- ✓ **የአጀንዳው ጭብጥ**

  የጭብጡ ማጠቃለያ በራሱ እንደ አንድ ሰነድ ሆኖ ለማሰራጨት በሚመች መልኩ መታተም አለበት

- ✓ **ማውጫ**

  የርዕስ ማውጫው አንባቢው የቢዝነስ አጀንዳውን እንደፈለገ ለማገላበጥ ይረዳዋል፡፡

- ✓ **መግቢያ**

  መግቢያው ስለ አጀንዳው ምንነት፣ ጥቅም፣ በዝግጅቱ እነማን እንደተሳተፉና ማን እንዳጸደቀው ማብራራት ይኖርበታል፡፡

- ✓ **ርዕሶች**

  እያንዳንዱ ርዕስ በንግድ ዘርፍ ወይም ክልል ተከፋፍሎ ስለተወሰኑ እንቅፋቶችና ፖሊሲ ነክ የመፍትሔ አስተያየቶች ማብራሪያ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ርዕስ የአትኩሮት ቡድን አወያይ ሊገኝ የሚችልበትን አድራሻና የቡድኑን አባላት ዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

- ግብረ ኃይሉ አጀንዳው ይፋ የሚሆንበትን ዕለት የሚገልጽ ጋዜጣዊ መግለጫ ማውጣትና የአጀንዳውን የጭብጥ ማጠቃለያ ለተሌቪዥን፣ ራዲዮና የሕትመት ማሰራጫ ጋዜጠኞች መበተን አለበት፡፡
  አጀንዳው በይፋ እስከሚቀርብበት ዕለት ድረስ ለጋዜጠኞች የተላከው ጋዜጣዊ መግለጫና የአጀንዳው ጭብጥ ማጠቃለያ ለህዘብ አይገለጽም፡፡ ማለትም አጀንዳው በይፋ ከሚቀርብበት ዕለት በፊት ዘጋቢዎች ስለይዘቱ የሚናገሩበት ምንም ነገር አይኖርም፡፡

## የአጀንዳው አቀራረብ ማመሳከሪያ

- ✓ የዋናው የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳ ቅጅ በዝግጅቱ ለተካፈሉት ሁሉ መስጠት አለበት፡፡
- ✓ ለመንግሥት ባለሥልጣናት የአጀንዳውን ቅጅ መስጠትና ለውይይት ቀጠሮ መጠየቅ ያሻል፡፡
- ✓ ለመገናኛ ብዙሃን የአጀንዳውን ቅጅ መላክና በይፋ ለማቅረብ ከተወሰነው ዕለት በፊት ምንም ዜና እንዳይወጣ ማድረግ

## ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፍረንስ ማዘጋጀት

- ✓ የመግለጫውን ቀንና ጊዜ መምረጥ
- ✓ መግለጫው የሚሰጥበትን ቦታ መምረጥ
- ✓ የአጀንዳውን ቅጅዎች፣ የጭብጥ ማጠቃለያውንና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት
- ✓ አጀንዳውን ለሚያቀርበው ግለሰብ ስለ እለቱ ዝርዝር ሁኔታ ማሳወቅ
- ✓ የሚዲያ ሰዎችንና ሌሎችንም ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖች መጋበዝ

- የፕሮጀክቱ ኮሚቴ ግብዣውንና ጋዜጣዊ መግለጫውን ለቢዝነስ ማኅበር መሪዎች በመላክ የግብዣውን ጥሪ ለአባሎቻቸው እንዲያስተላልፉ ማድረግ አለበት፡፡

- የአማካሪ ኮሚቴው ከአባላቱ መካከል አንዱን በመምረጥ የብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳውን ለርዕሰ መንግስቱ እንደያቀርብ ማድረግ አለበት፡፡

- አጀንዳውን የሚያቀረበው ሰው በጋዜጣዊ መግለጫው ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ምን እንደሆነ፣ ለግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ምን ዓይነት ጥቅም እንዳለው፣ ለብሔራዊ የኤኮኖሚ ደህንነት ያለው አስተዋጽኦ፡ ሰንት ማኅበራት በዝግጅቱ እንደተሳተፉና እንዳጸደቁት ማብራራት ይኖርበታል፡፡ የብሔራዊ ቢዝነስ አጀንዳው ለርዕሰ መንግስቱ ራሱን በቻለ ኦፊሲያላዊ ዕለት ሊቀርብላቸው ይችላል፡፡ ይህም ከቢሮ ኃላፊያቸው ጋር በመሆን መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በሆነ ምክንያት አጀንዳውን ለርዕስ መንግስቱ ማቅረብ ካልተቻለ ለሚመለከታቸው ሚኒስተሮችና ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ ኃላፊዎች መታደል ይኖርበታል፡፡

## አባሪ

***የተዋጣለት ጋዜጣዊ መግለጫ የመጻፍ መመሪያ***

*የፖለቲካና የኤኮኖሚ ለውጥ ለማምጣት ውጤታማ ከሚባሉት መንገዶች አንዱ ሕዝቡ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ማድረግ ነው:: የለውጥ ፈላጊነት የጋራ መግባባት እስኪገኝ ድረስ ይህን ለማድረግ ቀላሉና ብዙ ወጪ የማይጠይቀው ዘዴ አገልግሎት እየሰጡ ያሉትን የመገናኛ ብዙሃን በመጠቀም ነው:: ሆኖም እነዚህን የመገናኛ ዘዴዎች በብቃት ለመጠ ቀም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሚዲያ ዘዴዎች ጋር ጥርት ያለ የግንኙነት መስመር መዘርጋት አለበት:: የሚዲያ ሰዎችን ለማግኘት አንዱ ዘዴ በጋዜጣዊ መግለጫ አማካይነት ነው::*

***ጋዜጣዊ መግለጫዎች፤*** *ጋዜጣዊ መግለጫዎች መልዕክቶችን ለሚዲያ ሰዎች በማስተላለፍ እጅግ የተለመዱ መንገዶች ናቸው:: ሆኖም መግለጫዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የተወሰኑ መመሪያዎችን በመከተል መተግበር ይኖርባቸዋል:: የመመሪያዎቹ አስፈላጊነት ጋዜጣዊ መግለጫዎች ከተወዳዳሪ የዜና ትረካዎች የተለየ በመሆኑ ጋዜጠኞቹ ከፍ ባለ ፍላጎት እንዲያነቧቸው ስለሚረዱ ነው:: የአንድ የተዋጣለት ጋዜጣዊ መግለጫ የሚከተሉትን ባህሪያት ማሟላት ይኖርበታል::*

***ጥራት፤*** *የተወሰኑ ቁልፍ ጉዮች ለአንድ ጋዜጣዊ መግለጫን ለሚመለከት የሚዲያ ሰው ወዲያውኑ ቁልጭ ብለው ሊታዩ ይገባቸዋል:: በጋዜጣዊ መግለጫው አናት ላይ የድርጅቱ ስምና መለያ ምልክቱ መታየት ይኖርባቸዋል:: መግለጫው የተጻፈበት ቀለም የመገናኛ ማዕከል ከተባለው ግለሰብ ስምና የስልክ ቁጥር ጋር እንዲሁ ከላይ መጻፍ ይኖርባቸዋል:: ጋዜጣዊ መግለጫው የዘቱን አጥር አድርጎ ሊያመላክት የሚችል ግልጽ ርዕስ ሊኖረው ይገባል:: የመግለጫው ይዘት ቀደሞ ሊረዳቸው ካልቻለ ዘጋቢዎች የተላከላቸውን ጽሁፍ አያነቡትም::*

***ድፍረት፤*** *ጋዜጣዊ መግለጫዎች ከአንድ ገጽ የማይበልጡ መሆን አለባቸው:: ከአንድ ገጽ እስካልበለጠ ድረስ አቀራርቦ መጻፍ የሚቻል ቢሆንም ቅሉ ተመራጭ የሚሆነው በሁለት መስመር ክፍተት ሲጻፍ ነው:: በጋዜጣዊ መግለጫው ሁሉንም አመለካከት ለማካተት የመፈለግ ተፈጥሮአዊ አዝማሚያ አለ:: ነገር ግን የአመለካከትን ይዘት ደረጃ ማውጣትና አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ብቻ በመግለጫው ማካተት ያስፈልጋል:: የጋዜጣዊ መግለጫ ጥቅሙ ዋንኛ የሆኑ መረጃዎችን መስጠትና ጋዜጠ ኞች ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲጠይቁ ለማበረታታት / ለመገፋፋት / ነው::*

***ዝርዝሮች፤*** *በጋዜጣዊ መግለጫ የትኞቹ ቁልፍ መረጃዎች ይካተቱ ብሎ መወሰን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: መከተል የሚገባን ምን ለማለት ነው የተፈለገው?፣ ማን ነው ምን ማለት የፈለገው? የት ነው ጉዳዩ የተፈጸመው? መቸ? ለምን ጥቅም ሲባል? የሚሉትን ነጥቦች ነው:: ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስ ላያስፈልግ ይችላል:: ነገር ግን ምንም ነገር ሳይካተት እንዳልቀረ ለማረጋገጥ ሲባል እንደዚህ ያሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ስለጉዳዩ መለማመድ ያሻል:: እጅግ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በማካተት እያንዳንዱን ጥያቄ መመለስ ይገባል::*

***አዘገጃጀት /ቅርጽ/፤*** *ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው ጋዜጣዊ መግለጫ ደረጃውን የጠበቀ አቀራረጽ መከተል አለበት:: በተቻለ መጠን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ማኅበረተሰብ ወይም ድርጅቶች መሪዎች አባባሎች የተገኙ አጫጭርና ጠቃሚ ጥቅሶችን በመጀመሪያው ወይም ሁለተኛው አምድ ላይ መጥቀስ ጠቃሚ ነው::*

የመግለጫው የመጨረሻ አምድ ስለ ድርጅቱ አጭር ማብራሪያ ለመስጠት መዋል አለበት፡፡ በመጨረሻ ጋዜጣዊ መግለጫው የሚቋጨው ለጋዜጠኞች ተጨማሪ የመረጃ ገጾች አለመኖራቸውን የሚያሳይ ምልክት በማኖር ይሆናል፡፡ በአሜሪካን ሀገር የመግለጫው መጠናቀቅን ለማሳየት በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉት ምልክቶች -30- ወይም # # # ናቸው፡፡

<u>የጋዜጣዊ መግለጫ ናሙና</u>

ዓለም አቀፍ የግል
ኢንተርፕራይዝ ማዕከል

ሣይፕ

የሚዲያ አማካሪ

የማደሰን ቢሮ ህንጻ
1155፣ 15ኛ መንገድ ኤን ደብሊው,
ሱዊት 700
ዋሽንግተን ዲሲ
ስልክ 202/721/-9200
ፋክስ 202/721-9250
WWW.CIPE.Org
ጆርግ አምሴለን
በስልክ ቁ /202/721-9225 ያግኙ

በፍጥነት የሚሰራጭ
ኖቨመበር 19 2001 እ.ኢ.አ

የሰርቢያ ቢሮክራሲ ደሞክራሲያዊ ለውጥን ያውካል፡፡

ዋሽንግተን ዲሲ፣ የዓለም አቀፍ ኢንተርኘራይዝ ማዕከል(ሣይፕ) ቤልግሬድ ውስጥ ከሚገኘው የጂ.17, ድርጅት ጋር በመሆን ሰርበያ ውስጥ ስለሚገኘው የኤኮኖሚ ዘርፍና አውዳሚ ስለሆነው ቀረጥና እያደገ ስለመጣው የቢሮክራሲ ማነቆ ጥናት ያደርጋል፡፡ ያልተደራጀው የስርቢያ የኤኮኖሚ ዘርፍ ከሀገሪቱ አጠቃላይ ምርት ሀመሳ በመቶው መሆን ከጀመረ ቆይቷል፡፡ ኮም አር ሆልምስ የሄሪታጅ ፋውንደሽን ኘሬዚዳንትና የሣይኘ የቦርድ አባል እንዳሉት እጅግ የተጋነነው ቁጥጥር ያስከተለው ወጪ ሕጋዊ አምራቹን እንዲሰወርና ወደ ያልተደራጀው የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲያሰማራ፣ በሰርብያ የዴሞክራሲያዊ አመራር እምነት እንዲዳክምና የግሉ አምራች ኃይል ከኤኮኖሚና የፖለቲካ ለውጥ አራማጅነትም እንዲሸሽ አድርጎታል፡፡

ሳይፕና የጂ-17 ኢንስቲትዩት የሰርቪያን የንግድ እንቅስቃሴ በስፋት የሚዳስስ ጥናት ያደርጋሉ፡፡ ውጤቱንም ይወያዩበታል፡፡ ይፋ ያደርጉታል፡፡ ፕሮጀክቱ መንግስት በነፃው ገበያ ጣልቃ መግባቶ የሚያስከትለውን ወጪ ያልተደራጀውን የኤኮኖሚ ዘርፍ የማስፋፋት ውጤት ያለው መሆኑን አጉልቶ ችግሩ የህዝብ ግንዛቤን እንዲያገኝ በማድረስ ያሳያል፡፡ የፖለቲካ ለውጥ የማምጣት የብሔራዊ አጀንዳ ለማውጣትም ይረዳል፡፡

ይህ ፕሮጀክት ሊተገበር የቻለው ከናሽናል ኤንቨስትመንት ፎር ዴሞክራሲ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ሣይፕ የግል ባለሀብቱን በማካተት የውስጥ ፖሊሲ፣ የተቋማት የአደረጃጀት ማሻሻያ፣ የህዝብ አስተዳደርን ማሻሻልና በነፃ ገበያ ላይ የተመሰረተ የዴሞክራሲ ግንባታ በሚሉ ርዕሶች በ80 ሀገራት ውስጥ 700 የሚሆኑ ብሔራዊ የለውጥ ተነሳሽነቶችን ደግፏል፡፡ ሣይፕ አትራፊ የልሆነ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የንግድ ም/ቤት አካል ነው፡፡

**ዕለቶች፤** አንድ ጋዜጣዊ መግለጫ አንድ ዕለትን ለማሳወቅ ከጥቅም ላይ ከዋለ ለሚዲያ የሚላከው እንደ ግብዣ ጥሪ ሆኖ ነው፡፡ ነገር ግን ከግብዣ ጥሪነት በተለየ መልኩ በአጀንዳ ዝግጅቱ የተካፈሉ አባላት በጋዜጣዊ መግለጫው ሊካተቱ የሚገባቸውን ነገሮች እንዲያሳውቁ ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡ የግብዣ ጥሪው የጋባዥን ስም፣ የድርጅቱን የመለያ ምልክትና እንዲሳተፉ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡ ወይም / የአንድ የሚመለከተውን ቁልፍ ግለሰብ ስም በመጥቀስ / እንዲሳተፉ ጋብዞዎታል የሚሉትን ያካተተ መሆን ይኖረበታል፡፡ የዕለቱ የመለያ መጠሪያ የሚከናወንበት ቀን ሰዓትና ቦታም ጎላ ብሎ ተጽፎ መከተል አለበት፡፡ ዕለቱ ለምን ጠቃሚ እንደሆነ በነጠላ መስመር የተጻፈ አንድ አምድ የክብር እንግዳውን ስም ማዕረግና እለቱ ለምን ጠ ቃሚ እንደሆነ ለመግለጽ መዋል አለበት፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫው ለሚነሱ ጉዳዮች ሁሉ መገኘት ያለበትን ሰው አድራሻና እባክዎትን መልስ ይስጡን በማለት ማጠ ቃለል አለበት፡፡

## ስለ ስርጭርት

**ማስታወሻ፤** ጋዜጣዊ መግለጫ በሚሰራጭበት ጊዜ ተለይተው ለታወቁ ጋዜጠኞች በስም ለመላክ መሞከር አለበት፡፡ የአንድ እለት ማስታወቂያ እለቱ ከሚከናወንበት አንድ ሳምንት በፊት ለማስታወስ እንደገና በላክ ተገቢ ነው፡፡ ጋዜጠኞችን በመጋበዝ በመግለጫው ላይ እንዲያተኩሩ በመደረጉ ፍራቻ ሊኖር አይገባም፡፡ መግለጫው ለኅትመትና የአየር ማሰራጫ ሚዲያዎች ለሁለቱም መላክ አለበት ከጊዜ በኋላ በተደጋጋሚ ሲዘግቡ ከቆዩ ጋዜጠኞች ጋር ቅርብ ግንኙነት በመመስረት አስተማማኝ የዜና / መረጃ ምንጫቸው ለመሆን ይችላል፡፡

## የተከፈለው

**ሚዲያ፤** አብዛኛውን ጊዜ የጋዜጠኞችን የነጻ አገልግሎት መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ሚዲያዎች የህዝብን አመለካከት ለመለወጥ ወሳኝ መንገዶች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን እንደአስፈላጊነቱ ለሚዲያ አገልግሎት ዋጋ ሊከፈል ይችላል፡፡ በአንዳንድ ሀገራት ጥቂት ዘጋቢዎች አንድ ጉዳይ ለማተም ክፍያ ይጠይቃሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ባለደረሰኝ ጋዜጠኝነት ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ ሊወገድ ይገባዋል፡፡

**<u>የግብዣ ጥሪ ናሙና</u>**

| | | |
|---|---|---|
| **የዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል** | **ሣይፕ** | **የሚደስን ቢሮ ህንጻ** 1155 15**ኛው መንገድ ኤን.ደብሊዩ ሉዊት** 700**፣ ዋሽንግተን ዲሲ**<br>202/721-9200 /**ስልክ**/<br>202/721-9250 /**ፋክስ**/<br>WWW.CIPE.ORG |

**ዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል ለሰላምና፣ ዴሞክራሲና የገበያ ኤኮኖሚ፤**

**በሚል እሮብ ኖቬምበር** 7,2001 **ከ**3፡00-5፡00 **ጠዋት** 1155 15**ኛው መንገድ ኤን ደብሊው ስዊት** 700 **ዋሽንግተን ዲሲ** 20005 **በሚያካሄደው ውይይት ላይ እንዲገኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡**

**ስም** ................................................ **ኤሜል** ...................................................

**ድርጅት**.............................................................. **የስልክ ቁ** ........................................

# የ21ኛው ምዕት ዓመት
# የቢዝነስ ማኅበራት

## የወደፊቱ ንድፍ

የዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይስ ማዕከል

ዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይስ
የዩ.ኤስ. የንግድ ምክር ቤት አካል ነው

ሳይፕ

የሣይፕ አባላት /ሠራተኞች

| | |
|---|---|
| 1. ዶኖሁ፣ ቶማስ ጄ | ፕሬዚዳንት |
| 2. ወርክማን ፣ ዊላርድ ኤ | ምክትል ፕሬዚዳንት |
| 3. ሱሊቫን፣ ጃህን ዲ | ዋና ዳይሬከተር |
| 4. አምሴለ፣ ጀርግ | የዳይሬክተር ጉዳይ አስፈጻሚ |
| 5. ብሩንሶን፣ ካሬን | የገንዘብ ምክትል |
| 6. ሳሌባውት ጆህን ጀ | የፕሮግራም ኦፌሰር /ኤሲያ/ |
| 7. ፕኤንኤር፣ ጀኒፈር አር | የመገናኛ መኮንን |
| 8. ኮስታ፣ ሊየን | የማሰልጠኛ ፕሮግራም ኦፊሰር |
| 9. ዴከር ሲይልዴሊን | ዋና ምክትል |
| 10.ሆሳኢን ታሪን | የፕሮግራም ምክትል / ኤሲያ / |
| 11. ከምፕማን፣ ካቲ | የፕሮግራም ኦፌሰር / አፍሪካ/ |
| 12.ኩችታ ሄልብሊንግ፣ ካተሪን | የፕሮግራም ኦፌሰር / ላቲን አሜሪካ/ የምርምርና የወክልና ኦፊሰር |
| 13.መንግስቱ አማኑኤል | የፕሮግራም ምክትል / አፍሪቃ/ |
| 14.ሞለር ካራ፣ ኢ | የድጋፍና መረጃ ኦፊሰር |
| 15.ሞትሌይ፣ ታሜራ | አስተናጋጅ |
| 16.ናደል፣ ሂክ | የፕሮግራም ኦፊሰር /መካከለኛው ምስራቅ አፍሪቃ/ |
| 17.ፔሶላኖ፣ ካዝሊን ኤም | የፕሮግራም ምክትል / ላቲን አሜሪካ/ |
| 18.ሮች ጌል | የምክትል ፕሬዚዳንት፣ የአስተዳደር ምክትል |
| 19.ሮጀርስ ጂን | የፕሮግራሞች ም/ዳይሬክተር |
| 20.ሮጀርስ፣ ስቴቨን ቢ | የአፈጻጸምና የፖሊሲ ለውጥ ም/ዳሬክተር |
| 21.ሳኪአን፣ ሮቢይን | የዩሮ-ኤሲያ የፕሮግራም ኦፊሰር |
| 22.ሳውዝወርዝ፣ ዳና | የመካከለኛው አውሮፓና የዩሮ-ኤሲያ የፕሮግራም ኦፊሰር |
| 23.ሱሂር ኤሌና | የዩሮ-ኤሲያ/ማዕከላዊ ኤሲያ የፕሮግራም ኦፊሰር |
| 24.ሱንግ፣ ጂን | የድጋፍ አፈጻጸምና መረጃ ምክትል |
| 25.ዋትኪንስ፣ ዴኒስ | የፋይናንስ ማናጀር |
| 26.ዋልሰን፣ አንድሩው | ከፍተኛ የፕሮግራም ኦፊሰር / መካከለኛ አውሮፓና ዩሮ-ኤሲያ / |
| 27.ዩን ኦክሳና | የዩሮ-ኤሲያ የፕሮግራም ምክትል |
| 28.ዜምኮ ጆህን ኤ | ከፍተኛ የፕሮግራም ኦፊሰር / ላቲን አሜሪካና / የመገናኛዎች ዳሬክተር |

**የግብፅ ጽ/ቤት**
ራንዳ አል ዘግህቢ
የፕሮግራም ዳሬክተር

**የኮሶቮ ጽ/ቤት**
ቪቬክ ዴት
የፕሮጀክት ማናጀር

**የሞንቴ ኔግሮ ጽ/ቤት**
ራልፍ ማላት
የፕሮጀክት ማናጀር

**የሮማኒያ ጽ/ቤት**
ማርክ ማክኮርድ
የፓርቲ አዛዥ

**<u>የሩሲያ ጽ/ቤት</u>**
ኤሌና ሞዝሄኮ
ተባባሪ ዳሬክተር

በኢትዮጵያ የሳይፕ ፕሮጀክት አጋር ተቋሞች
**<u>የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት</u>**
አቶ ጋሻው አባተ የፕሮጀክት አስተባባሪ
አቶ ፋሲካ ጅፋር የፕሮጀክት አማካሪ ቦርድ ጸሐፊ

**<u>የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት</u>**
አቶ ተፈሪ አስፋው የፕሮጀክት አማካሪ ቦርድ አባል

**<u>የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማኅበር</u>**
ዶር አሰፋ አድማሱ
የፕሮጀክት አማካሪ ቦረድ አባልና
የፕሮጀክት የቴክኒክ ግብአቶች ዋና አስተባባሪ

**<u>የነጥቦች ማስታወሻ</u>**

**<u>የነጥቦች ማስታወሻዎች</u>**

| |
|---|
| **አለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይስ ማዕከል** |

**ፌልግ** የኤኮኖሚ ለውጥ ዛሬ፤ ወሳኝ የግሎባላይዜሽን ጉዳዮች

**<u>የሳይፕ አውነተኛ የቢዝነስ ተቋማት ገጽ</u>**

| | |
|---|---|
| ጸረ ሙስና | **<u>የኤኮኖሚ ነጻነት መድረክ</u>** የሳይፕ የቀጥተኛ መስመር የመረጃ አገልግሎት ከሰባ በሚበልጡ አገሮች የዲሞክራሲንና ነጻ ገቢያን ለማራመድ የተነደፈ |
| የሴቶች ጉዳዮች | • የኢኮኖሚ ነጻነት ኔትወርክ በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ የሳይፕ አጋሮች ጋር ያገናኛል:: |
| የኮርፖሬት አመራር | • ዓለም አቀፍ የኮርፐሬት አመራር መገንባት |
| የሳይፕ ዓለም አቀፍ አገሮች | • ሙስናን መዋጋት<br>• የሩሲያኛና ዓረብኛ ድረ ገጾች |

**WWW. CIPE.Org.**


1የአማርኛ ቅጅ

የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 የቤት ቁጥር 550

ስልክ 251115518240/ 5514005 ፋክስ 251115517699
ኢሜል ethchamb@ethionet.et ድረ ገጽ WWW Ethiopianchamber.com